# ከኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል

## ጋር በመተባበር በየሳምንቱ የሚታተም

# የቁርጠኝነትና ተናበ የመሥራት ውጤት

የወላይታ ዞን ለሀገር ልማት ቁልፍ አበርክቶ ያላቸው የጊቤ 3 የውሃ ኃይል ማመንጫ ጣቢያ፣ የወላይታ ሶዶ ባለ 500 ኪሎ ቮልት ኮንቨርተር ሰብስቴሽን እና ከሦስት ኃይል ማመንጫ ጣቢያዎች የሚቀበለው የሶዶ ቁጥር ሁለት ኃይል ማከፋፈያ ጣቢያ የሚገኝበት እንዲሁም የኢትዮ- ኬንያ ከፍተኛ ኃይል ማስተላለፊያ መስመር የሚያቋርጥበት ወይም ትላልቅ የኤሌክትሪክ መሠረተ ልማቶች የሚገኙበት አካባቢ ነው።

ኢትዮጵያ ልክ እንደ ቆዳ፣ ሌጦና ጥራጥሬ ሁሉ የኤሌክትሪክ ኃይል ምርትን ለውጭ ሀገራት ማቅረብ ከጀመረች ሰነባብታለች። የወላይታ ሶዶ ባለ 500 ኪሎ ቮልት ኮንቨርተር ሰብስቴሽን እና የኢትዮ- ኬንያ ከፍተኛ ኃይል ማስተላለፊያ መስመር ለውጭ አገራትን የኃይል አቅርቦት ሥራ በአስተማማኝ ሁኔታ ለማሳለጥ ታስበው የተገነቡ የኤሌክትሪክ መሠረተ ልማቶች ናቸው። ይሁንና ግላዊነት እንጂ ሀገራዊ ዕድገትን የማይሹ ራስ ወዳዶች፤ ከባድ አገራዊ ውድመት ፈጽመው ጥቂት ማግኘት የሚፈለጉ ጥቅመኞች፤ በኃይል ማስተላለፊያ መስመር ተሸካሚ የብረት ምሰሶዎች ላይ ተደጋጋሚ ስርቆት አድርሰዋል። በዚህ የስርቆት ድርጊትም ተቋሙን ለከፍተኛ ኪሳራ ዳርገውታል። ይህን አስመልክቶ የኢትዮ- ኬንያ ኢንተር ኮኔክሽን ፕሮጀክት የሳይት ሥራ አስኪያጅ ኢንጂነር ቴዎድሮስ አያሌው የሰጡንን መረጃ ባለፈው ሳምንት ማስነበባችን ይታወሳል።

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ግን በዞኑ ይታይ የነበረው የስርቆት መጠን ቀንሷል። የዚህ ምክንያት ተቋሙ ከአካባቢው ነዋሪዎችና ከቀበሌ እስከ ክልል ካሉ መስተዳድሮች ጋር ችግሩን ለማስወገድ ያደረገው ያላሰለሰ ጥረት ነው። ውድ አንባቢያን ተቋሙ ከአካባቢው መስተዳድር አካላት ጋር ያከናወናቸው ተግባራት ለሌሎች አካባቢዎችም መልካም ተሞክሮ መሆን ይችላሉ በሚል የዛሬው ጽፅሁፋችን ማጠንጠኛ አድርገን አቅርበነዋል፣ መልካም ንባብ።



ዋና ኢንስፔክተር ጎዎ ቱሳ (ፒ.ኤች.ዲ)

የወላይታ ዞን ፖሊስ አዛዥ ዋና ኢንስፔክተር ጎዎ ቱሳ (ፒ.ኤች.ዲ) እንደሚገልፁት ከ2010 ዓ.ም ጀምሮ በኤሌክትሪክና በቴሌ ኮሙዩኒኬሽን መሠረተ ልማቶች ላይ ባልተለመደ ሁኔታ ስርቆት ይፈጸም ነበር። ስርቆቱን ለማስቀረት ምን መደረግ አለበት? የዞኑ ፖሊስ መምሪያ ድርሻ ምንድነው? የሚሉ ጉዳዮችን በጥልቀት መገምገም የመጀመሪያው ተግባር ሲሆን በቡድንም ይሁን በተናጠል በመሰረተ ልማት አውታሮችላይ ስርቆት የሚፈፅሙትን አካላት ማወቅ የሚያስችል ግብረ ኃይል እና የምርመራ ቡድን አደራጅቶ ወደ ሥራ መግባት ደግሞ ሁለተኛው ተግባር ነበር። በወቅቱ ከዚሁ ጉዳይ ጋር ተያይዞ የቆዩ የክስ መዝገቦችን ጭምር እንደገና በማንቀሳቀስ ተጠርጣሪዎች የማደን ሥራም ተሠርቷል።

ተጠርጣሪዎች አስተማሪ ቅጣት እንዲያገኙ ከማድረግ አንጻርም በፖሊስ፣ በአቃቤ ሕግና በፍርድ ቤቶች ላይ ይስተዋሉ የነበሩ ክፍተቶች ተገምግመው ማስተካከያ ተደርጎባቸዋል። ባለድርሻ አካላት ስርቆቱን እንደተራ ጉዳይ ከመመልከት አስተሳሰብ ወጥተው ሁሉም የየራሳቸውን ኃላፊነት በጥብቅ ዲሲፒሊን እንዲመሩ ተደርጓል። ንብረቱን የሚያስተዳድሩ ተቋማትም የተሰረቀባቸውን ንብረት በወቅቱ እንዲያሳውቁና በሕግ ሙያተኞቻቸው አማካኝነት ክሳቸውን እንዲከታተሉ በመደረጉ በርካቶቹ ክሶች ውሳኔ አግኝተዋል። በዚሁ መሰረት ተከሳሾች እንደወንጀላቸው መጠን ከስድስት ወር እስከ አስራ አራት ዓመት የሚደርስ የእስር ቅጣት የተወሰነባቸው መሆኑን ዋና ኢንስፔክተሩ ተናግረዋል።

የስርቆት ወንጀል ፈጽመው ወደ ሞያሌ እና አዲስ አበባ ሄደው የተሸሸጉ ተጠርጣሪዎችን ሳይቀር ተከታትሎ በመያዝ ቅጣታቸውን እንዲቀበሉ ተደርጓል። ፖሊስ ጠንካራ ክትትል በማድረጉ፣ አቃቤ ሕግም ተገቢውን ክስ መስርቶ ወንጀለኞችን ተጠያቂ በማድረጉና ዳኞችም ተገቢውን ውሳኔ በመስጠታቸው አበረታች ውጤት ታይቷል ይላሉ።

መሠረተ ልማቶችን እንደራሱ ንብረት የመጠበቅና የመቆጣጠር ኃላፊነትም ለአካባቢው ማህበረሰብ ተሰጥቶታል ያሉት ፖሊስ አዛዡ ቀደም ሲል በአንድ ግለሰብ ማሳ ላይ የቆመን የኤሌክትሪክ ማማ ይቆጣጠር የነበረው ባለማሳው ብቻ ነበር። የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራዎች ከተሠሩ በኋላ ግን ዙሪያ ገባውን የሚቃኝና ጉዳዩ የእኔ ነው የሚል አመለካከት ያለው ማህበረሰብ በመፈጠሩ ንብረቱን በባለቤትነት ተረክቦ ከስርቆት እንዲጠብቅ አስችሏል ብለዋል።

በዞኑ ከፍተኛ ስርቆት የተፈጸመባቸው አምስት ወረዳዎችም ተለይተዋል። ከነዚህ ውስጥ አንዱ የጊቤ ሦስት መገኛ የሆነው ኪንዶ ዲዳዬ ወረዳ ነው ። ይህ ወረዳ ከጋሞ ዞን ቁጫ ወረዳ ጋር የሚዋሰን በመሆኑ ወንጀለኞች ወደዚህና ወደዚያ እየተንቀሳቀሱ ወንጀል የሚፈጽሙበት ነው። ያም ሆኖ የሁለቱም ዞን ፖሊሶች በቅንጅት በመሥራት እና የአካባቢው ማሕበረሰብ በሚያደርገው ጥቆማ ወንጀለኞችን መያዝ ተችሏል።

በዚህ ወረዳ አሥር የክስ መዝገቦች ተደራጅተው በ22 ተጠርጣሪዎች ላይ ክስ ተመስርቶ አስር ግለሰቦች ላይ ከአምስት እስከ አራት ዓመት የጽኑ እስራት ቅጣት ተወስኗል። በዳሞት ጋሌ ወረዳ በሶስት የክስ መዝገቦች ዘጠኝ ሰዎች ላይ፣ ዱጉና ፋንጎ ወረዳ በሶስት ሰዎች ላይ ፤ በወላይታ ሶዶ ዙሪያ በስምንት ሰዎች ላይ ፤ በወላይታ ሶዶ ከተማም በሁለት ተጠርጣሪዎች ላይ ክስ ተመስርቶ ምርመራ እየተጣራ መሆኑን ገልጸውልናል። የሚሰረቁ ንብረቶች አንዳንዶቹ መዳረሻቸው የወዳደቁ ብረቶችን በሚሰበስቡ ግለሰቦች ቤት እንደሆነ ተደርሶበት ፈቃድ እስከ መሰረዝ የደረሰ ርምጃ መወሰዱን ዋና አዛዡ ነግረውናል።

በህዝብ ከፍተኛ መዋዕለ ንዋይ የተገነቡ ትላልቅ መሠረተ ልማቶችን በስርቆት ምክንያት ሲወድሙ ማየት ሁሉንም የፖሊስ አባላት ክፉኛ የሚያስቆጭ ተግባር መሆኑን የተናገሩት ዋና ኢንስፔክተር ጎዎ ቱሳ (ፒ.ኤች.ዲ) የመስተዳድር አካላትና ማህበረሰቡ በቁርጠኝነት ተናቦ መሥራት መቻሉ የሥርቆት ወንጀሉ እንዲቀንስ አስችሏል ይላሉ። ይህን መሰል አሠራራርም በሁሉም አካባቢዎች መሥራት ከተቻለ የሥርቆት ወንጀልን መቀነስ ብሎም መቆጣጠር እንደሚቻል ልምዳቸውን አካፍለውናል።

የመሠረተ ልማት ስርቆት በአገር ህልውና ላይ የተጋረጠ ትልቅ አደጋ መሆኑን የተናገሩት ዋና ኢንስፔክተሩ በየትኛውም አካባቢ የሚገኝ የፖሊስ ተቋም ከማህበረሰቡ ጋር ተቀናጅቶ ከሠራ ሥርቆትን አስቀድሞ መከላከል እንደሚቻል ተሞክሯቸውን አካፍለውናል።

የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል